www.abyssinialaw.com

# የኢትዮጵያ የገጠር ወጣቶች
# የእድገት ፓኬጅ

www.abyssinialaw.com

# ማውጫ፣

ርዕሶች ገጽ

መግቢያ ........................................................... 1

ክፍል አንድ

የኢትዮጵያ ወጣቶች የሚገኙበት ሁኔታ ........................... 5

1.1. ስራ አጥነት የወጣጡ አንገብጋቢ ችግር ነው ..................... 5

1.2. ብቁ የማህበራዊ አገልግሎትና የመዝናኛ ማእከላት እጦት
መፈታት ያለባቸወ የወጣቱ አንገብጋቢ ጥያቄዎች ናቸው። .... 9

1.3. ወጣቱ ተሳትፎውን በሰፊው የሚያረፉግጡ
መድረኮች ይሻል፣ ............................................... 11

ክፍል ሁለት

የአትዮጵያ ወጣቶች ራእይና ስትራቴጂ፣ ........................... 13

1. የወጣቶች የልማትና የእድገት ራእይ፣ ............................. 13

2. የወጣቱን ጥያቄዎች ስመመለስ የምንከተላቸው................. 13

ስትራቴጂካዊ አቅጣጫዎች፣........................................... 13

ያአል ሶስት

የገጠር ወጣቶችን እድገትና ተጠቃሚነት
ስማረጋገጥ የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፣ ......................... 21

**1. የገጠር ወጣት ጥያቄዎች መመስስ፣ ..................................... 21**

ያአል አራት

በፓኬጁ ትግበራ ክትትልና ግምገማ
የወጣቱና የመንግስት ሚናና ድርሻ፣.................................. 46

1. በፓኬጁ ትግበራ፣ ክትትልና ግምገማ
የወጣቶች ሚናና ድርሻ ................................................ 46

2. በፓኬጁ ትግበራ፣ ክትትልና ግምገማ ረገድ
የመንግስት ሚናና ድርሻ .............................................. 50

## መግቢያ፣

ከ75 ሚሊዮን ያህል ህዝባችን ውስጥ ከ15-29 አመት እድሜ ያለው ወጣት የህብረተሰብ ክፍል 21.16 ሚሊዮን (30%) ያህል ነው:: ይህ ቁጥር ከህብረተሰቡ ቁጥር መጨመር ጋር ተያይዞ እየጨመረ እንደሚሄድም ይጠበቃል::

ወጣቱ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ከመሆኑ በተጨማሪ በህብረተሰባችን ውስጥ ዋነኛው አምራች ሃይልም ነው:: በገጠርም በከተማም እንደሁኔታው ቀዳሚው ወይም ተከታዩ የቤተሰብ የገቢ ምንጭ ነው:: ሰፊ ህፃናትና አረጋውያን ባሉበት ህብረተሰብ እነዚህን ክፍሎች ጨምሮ የሚሸከመው ወጣቱ አምራች ሃይል ነው:: ይህ እውነታ ብቻውን ተወስዶ ሲታይ እንኳ ህብረተሰባችን ለወጣቱ ዙሪያ መለስ ግንባታ ልዩ ትኩረት መስጠት እንዳለበት ያመላክታል::

የአገራችን ወጣቶች በመገንባት ላይ ባለው ስርአት ሊጫወቱት የሚችሉትና የሚጫወቱት ሚና ትልቅ መሆኑ እንደተጠበቀ የመጪው ስርአት ተረካቢዎች መሆናቸውም ለወጣቱ ልዩ ትኩረት መስጠትን የሚጠይቅ ነው:: ወጣቱ በተያያዝነው የአገር ግንባታ ተገቢ ሚናውን ከመጫወት ባሻገር የራሱን ዘመን በትክክል ለመምራትም መዘጋጀት ይኖርበታል:: በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ግልፅነት ያለው፣ በአገር ግንባታ ንቁና የተደራጀ ተሳትፎ ያለውና ተጠቃሚነቱ የተረጋገጠ ወጣት ሆኖ ሊገነባና በዚህም ሂደት አገሩን እየለወጠ ራሱም ሊለወጥ የሚችልበትን ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል:: በመሆኑም ወጣቱን ለቀጣዩ የዳበረ

ዴሞክራሲያዊ ስርአት ተረካቢነት ለማዘጋጀት ለወጣቱ ልዩ ትኩረት መስጠት የሚጠይቅ ሆኖ ይገኛል፡፡

ወጣቱ የአሁኑ ገንቢ የነገው ተረካቢ መሆኑ ባያጠያይቅም በመንግስት ሆነ በህብረተሰብ ደረጃ ለወጣቱ ግንባታ የተሰጠው ትኩረት እጅግ አናሳ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ምንም እንኳ መንግስት በአጠቃላይ ህብረተሰባችንን በለውጥ ጎዳና ለመምራት ባደረገው የተሳካ ጥረት ወጣቱም ተጠቃሚ መሆን እንደጀመረ ባይካድም በወጣቱ ዘንድ ከሚታዩ የተከማመሩ ችግሮች በመነሳት ራሱን ወጣቱን ዋነኛ ችግር ፈች ሃይል አድርጎ በማንቀሳቀስና የወጣቱን ጉዳይ በዋነኛ አጀንዳነት መድቦ በመንቀሳቀስ ረገድ እምብዛም እንዳልተሰራ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በቅርቡ በየክልሉ የገጠርና የከተማ ወጣቶችን ችግሮች ከራሳቸው ከወጣቶች ጋር በተካሄደ ውይይት ለማጥናት በተደረገው ጥረት የተገኙት እውነታዎችም ይህን ሃቅ በጉልህ ያሳያሉ፡፡ በከተማም በገጠርም ወጣቶች የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የፖለቲካዊ ችግሮች አላላውስ እንዳሏቸው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከዚህም የመነጨ የመገለልና የተስፋ መቁረጥ መንፈስ እንደዋጣቸው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ የዛሬውን አገር ገንቢና የነገውን አገር ተረካቢ ወጣት የመገለልና ተስፋ መቁረጥ ስሜት ከዋጠው የዴሞክራሲና የዳበረ የነፃ ገበያ ስርአት ግንባታ ጥረታችን ከፍተኛ ፈተና ይገጥመዋል፡፡ ይህ ፈተና ውሎ አድሮ የሚከሰት ሳይሆን በማንኛውም ቅርብ ጊዜ ሊከሰት የሚችልም ይሆናል፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የታዩትን ችግሮች ከነመንስኤያቸው በዝርዝር ተገንዝቦ በከፍተኛ የጥድፊያ መንፈስ መፍታት አማራጭ የሌለው ሆኖ ይገኛል፡፡

የኢትዮጵያ ወጣቶች የእድገት ፓኬጅ መቅረፅና በወጣቶችና በመላው ህብረተሰብ ተሳትፎ አጎልብቶ በፍጥነት በስራ ላይ ማዋል አስፈላጊ ሆኖ የተገኘው ከዚህ በመነሳት ነው፡፡ ይህ የኢትዮጵያ ወጣቶች የእድገት ፓኬጅ በ3 አበይት ምእራፎች ተደራጅቶ ቀርቧል፡፡ የመጀመሪያው ምእራፍ በወጣቱ ችግሮች ላይ ያተኩራል፡፡ ሁለተኛው ክፍል ራእይና ስትራቴጂያዊ ጉዳዮችን ያመላክታል፡፡ ሶስተኛው ክፍል ለወጣቱ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ዝርዝር መፍትሄዎችን ያቀርባል፡፡ በዚህ ፓኬጅ ትኩረት የተሰጠው በአርሶ አደር አካባቢዎችና በከተሞች ላይ ሲሆን በአርብቶ አደርና በከፊል አርብቶ አደር ክልሎች ለሚገኙ ወጣቶች የሚሆነው ፓኬጅ ከነሱ ሁኔታ ጋር ተጣጥሞ በዝርዝር እንዲቀረፅ ይደረጋል፡፡

በክፍል ሶስት የቀረበው መፍትሄ በገጠርና በከተማ ተከፋፍሎ ሲሆን ይህ አቀራረብ የተመረጠበት ምክንያት በገጠርና በከተማ የሚገኙ ወጣቶች ችግሮችና ከዚህም አኳያ የሚቀርቡት የመፍትሄ ሃሳቦች በአንዳንድ ገፅታዎች ተመሳሳይ ቢሆኑም በአብዛኛው የየራሳቸው የተለየ ባህሪ ያላቸው በመሆኑ ነው፡፡ በዚህ መልክ ተዘጋጅቶ የቀረበው የወጣቶች የእድገት ፓኬጅ በሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ተሳትፎ ዳብሮ በስራ ላይ እንዲሚውል ይጠበቃል፡፡

# ክፍል አንድ

## 1. የኢትዮጵያ ወጣቶች የሚገኙበት ሁኔታ፣

በአገራችን ከሚገኘው 21.16 ሚሊዮን የሚያህል ወጣት በ1997 ኢ.ም አመታዊ የስታትስቲክስ መፅሄት መሰረት 81.35% ያህሉ በገጠር ቀሪው 18.9% ያህሉ ደግሞ በከተሞች ይገኛል፡፡ ይህ አሃዝ ከገጠር ወደከተማ የሚደረገው ፍልሰት በፍጥነት በጨመረ ቁጥር እየተቀየረ እንደሚሄድ ለመገንዘብ ቢቻልም በገጠር ከፍተኛ የወጣት ክምችት መኖሩን ያመላክታል፡፡ በከተሞች የሚገኘው ወጣት በአንድ ማእከል ተከማችቶ የሚገኝ በመሆኑ ችግሩም የተከማቸ በመሆኑ በቀላሉ ሊታይና ሊታወቅ፣ መፍትሄም ሊፈለግለት ይችላል፡፡ ምንም እንኳ የተከማቸው የከተማ ወጣቶች ችግር በቀላሉ ሊታወቅ የሚችል ቢሆንም መፍትሄው የተራዘመ እንደሚሆን ይታመናል፡፡ በአንፃሩ በገጠር የሚገኘው ወጣት ብዛቱ ከፍተኛ ቢሆንም በአንድ ቦታ ተከማችቶ የሚገኝ አይደለም፡፡ በተነፃፃሪም በገጠር ለወጣቱ ችግሮች ፈጣንና በአጭር ጊዜ ብዙ ነገሮችን መቀየር የሚቻልበት መፍትሄ በተሻለ ፍጥነት ማቅረብ ይቻላል፡፡

## 1.1 ሥራ አጥነት የወጣቱ አንገብጋቢ ችግር ነው፣

በአገራችን ካለፉት 15 አመታት ወዲህ በተካሄደ የልማት፣ የዴሞክራሲና የሰላም ጥረት አገራችን መቀየር፣ ህብረተሰቡም መጠቀም ጀምሯል፡፡ ከዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ አኳያ ህገ መንግስታዊ ፌዴራላዊ ስርአት በመገንባቱና የዜጐችና የህዝቦች መብቶች ሳይነጣጠሉ በመከበራቸው፣ መንግስት በህዝብ ድምፅ የሚመረጥና ህዝብ ባልፈለገው

ጊዜም ሊቀይረው የሚችል መሆኑ፣ ሃሳብን የመግለፅ ነፃነት ተሟልቶ መከበሩና የዴሞክራሲ ተቋማት በብዛት መገንባታቸው ባለፉት 15 አመታት ከተመዘገቡት አበይት ፖለቲካዊ ድሎች መካከል ናቸው:: በኢኮኖሚው መስክ የእዝ ኢኮኖሚ ቀርቶ በምትኩ የነፃ ገበያ ስርአት በመገንባት ላይ ነው:: የመንግስት፣ የህዝብና የግሉ ሴክተር የኢኮኖሚ ሚናዎች በውል ተለይተው ሁሉም የኢኮኖሚ ተዋናዮች ሚናቸውን እንዲጫወቱ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል:: የአገራችን ኢኮኖሚ ጥራት ባላቸውና ለአገራችን ተስማሚ በሆኑ የኢኮኖሚ ፖሊሲና ስትራቴጅዎች የሚመራ በመሆኑ ባለፉት አመታት ከፍተኛ የእድገት ምጣኔ እያስመዘገበ በመጓዝ ላይ ነው:: ላለፉት አመታት በኤርትራ መንግስት ጠብ ጫሪነት ምክንያት ካጋጠመን የሁለት አመት ጦርነት ባሻገር አስተማማኝ ሰላም በማስፈናችንም የአገራችን ህዝቦች ከመቸውም ጊዜ የተሻለ እፎይታ አግኝተዋል::

ባለፉት 15 አመታት በልማት፣ በዴሞክራሲና በሰላም መስኮች ያገኘናቸው ድሎች መላ ህብረተሰባችንን ተጠቃሚ ማድረግ መጀመራቸው የህብረተሰቡ አካል የሆነውም ወጣት በየመስኩ በተገኘው መልካም ውጤት ተጠቃሚ እንደነበር ይታመናል:: በተለይ የአገራችን ወጣቶች በትምህርት መስክ ጥራቱ የተጠበቀና ሰፊ ስርጭት ያለው የትምህርት አገልግሎት እንዲያገኙ በተደረገው ጥረት ወጣቱ በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ በመሆን ላይ ነው:: ትምህርትን ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃዎች ለማስፋፋት በተደረገው ርብርብ ዛሬ በሁሉም ደረጃዎች ከ14 ሚሊዮን የማያንሱ ወጣቶች በትምህርት ገበታ ላይ

ይገኛሉ፡፡ በተዘረጋው የጤና መርሃ ግብርም ወጣቱን ጨምሮ መላው ህብረተሰብ ተጠቃሚ መሆን ጀምሯል፡፡ መንግስት ከነዚህ በተጨማሪ ለወጣቱ የሚሆን የወጣቶች ፖሊሲ በመቅረፅና የተቻለውን ያህል ተግባራዊ በማድረግ አበረታች ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ወጣቱ በሶስት መሰረታዊ ችግሮች ምክንያት ለችግር የተጋለጠ እንደሆነ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከነዚህም ችግሮች መካከል አንደኛው በተንሰራፋው ስራ አጥነት ምክንያት ወጣቱ የኢኮኖሚ ችግር ሰለባ መሆኑ፣ ሁለተኛው ለወጣቱ የሚሆኑ ብቁ የማህበራዊ አገልግሎቶች በተለይም የመዝናኛ ማእከላት እጦትና በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ የመገለልና የሚሳተፍበት መድረክ አለመመቻቸት ናቸው፡፡

በገጠርም በከተማም የሚገኘው ወጣት መሰረታዊ የሆኑ የኢኮኖሚ ጥያቄዎች አሉት፡፡ በገጠርም በከተማም ወጣቱ የስራ አጥነት ችግር እንደሚያሰቃየው ይገልፃል፡፡ በከተሞች የሚገኘው ወጣት ስራ አጥነት የሚመነጨው በአገራችን ለግል ሴክተሩ በተለይ ለአነስተኛ ጥቃቅን ተቋማት እድገት በር የሚከፍት ሁኔታ ተመቻችቶ ባለመቆየቱ ነው፡፡ ወጣቱ በራሱ ስራ እንዲፈጥር ለማድረግም ሆነ ሌሎች በፈጠሩት የስራ መስክ ተሰማርቶ ገቢውን እንዲያሻሽል፣ የግሉ ሴክተር በተለይም የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት መስፋፋት ይኖርባቸዋል፡፡ የመንግስት ፖሊሲ ልማትን የሚያበረታታ ሆኖ በዝርዝር ሊቀረፅና በተግባርም ሊውል ይገባዋል፡፡ የትምህርት ስርአቱም በአስተሳሰብና በሙያ ችሎታው የዳበረ ስራ ፈጣሪ ወጣት ሊፈጥር ይገባዋል፡፡ እነዚህ ከተሟሉና በተግባር ላይ ከዋሉ የወጣቱ የስራ አጥነት ችግር በተሻለ ፍጥነትና ስፋት ሊቀረፍ

የሚችል ቢሆንም በነዚህ መስኮች አገራችን ያደረገችው እንቅስቃሴ ዘግይቶ የጀመረና ብዙም ርቀት ያልተጓዘ በመሆኑ የከተማ ስራ አጥነት ችግር እንደተንሰራፋ ይገኛል::

ስራ አጥነት በከተሞች ብቻ የማይታጠር በገጠርም ሰፋ ባለ ደረጃ የሚታይ ችግር ነው:: የገጠሩ ወጣት የመሬት ጥያቄ ባለመመለሱ ወይም ደግሞ ባለው የመሬት ስሪት ውስጥ ወጣቱ የሚስተናገድበት ስርአት ባለመበጀቱ የገጠሩ ወጣት በንብረት አልባነት ስሜት የተዋጠ ነው:: በግብርናው መስክ የምንመራበት ፖሊሲና ስትራቴጂ ለብዙ ችግሮች መሰረታዊ መፍትሄ እያመጣ ቢሆንም በተሟላ መልኩ ባለመተግበሩም ሆነ በተወሰነ ደረጃ በሚተገበርበት ወቅት የወጣቱን ጥያቄ ግምት ውስጥ አስገብቶ በሚመልስበት አኳኋን ባለመቃኘቱ ወጣቱ የኢኮኖሚ ስጋቱ ከፍተኛ ነው:: ከግብርና ውጭ አማራጭ የስራና የገቢ እድል ባለመስፋፋቱ፣ ወጣቱ ከግብርናው በተጨማሪ ወይም ራሱን ችሎ ሌሎች አማራጮችን የሚሞክርበት እድል አልተመቻቸም::

በገጠርም በከተማም ያለው ወጣት የሙያ ክህሎቱን ለማሳደግ የሚያስችለው ስልጠና በሚፈለገው ስፋት አያገኝም:: በትምህርት ቤት ውስጥ ያሉትም ሆኑ ከትምህርት ውጭ ላሉት ወጣቶች የሙያ ስልጠና ፕሮግራሞች መቅረፅ አስፈላጊ እንደሆነ ቢታመንበትም እስካሁን በሰፊው የተስተናገደው ጥያቄ በትምህርት ገበታ 10ኛ ክፍልን ላጠናቀቁ ተማሪዎች ብቻ ነው:: ከ4ኛና ከ8ኛ ክፍል ትምህርት ለሚያቋርጡ ወጣቶችም ሆነ ቀደም ሲል ትምህርት ጨርሰው በስራ አጥነት ለተቀመጡ ወጣቶች የሚሆን የሙያ ስልጠና አልተጀመረም::

ወጣቱ በከተማም በገጠርም በስራ ፈጠራ እንዳይሳተፍ ከፍተኛ ማነቆ ሆነው ከሚገኙት ጉዳዮች አንዱ የፋይናንስ አቅርቦት አለመኖሩ ነው፡፡ ወጣቱ በራሱ ስራ እንዲፈጥር ለማድረግ ከስልጠና በተጨማሪ የተወሰነ መነሻ ገንዘብ ያስፈልገዋል፡፡ ይህን ገንዘብ በቀላሉ ከቤተሰቦቻቸው ለማግኘት የሚችሉት ወጣቶች ቁጥር እጅግ አነስተኛ ነው፡፡ አብዛኛው ከሌላ ምንጭ ካላገኘ በስተቀር በራሱ ሊያሟላው የሚችለው አይደለም፡፡ ይህ በዚህ እንዳለ መደበኛ ባንኮች ለወጣቱ በተለይ ለንብረት አልባ ወጣቱ የሚሆን የብድር ስርአት አላበጁም፡፡ አነስተኛ የገጠር ወይም የከተማ ባንኮች ደግሞ በአጠቃላይ ለህብረተሰቡ የሚሆን ብድር ከማቅረብ አልፈው ለወጣቱ የሚሆን ብድር የሚያቀርቡበት ስርአት አላመቻቹም፡፡ በዚህም ምክንያት የፋይናንስ ችግር ከሌሎች ዋነኛ ችግሮች ጋር ተደርቦ የወጣቱን የመስራት እድል አጥብቦታል፡፡ በአገራችን ከፍተኛ ቁጥር ያለውን ወጣት ሃይል ንቁና ተጠቃሚ የሆነ የኢኮኖሚ ተዋናይ ለማድረግ የሚካሄድ ማንኛውም ጥረት እነዚህንና መሰል ችግሮችን የሚቀርፍ ሆኖ መካሄድ ይኖርበታል፡፡

## 1.2 ብቁ የማህበራዊ አገልግሎትና የመዝናኛ ማእከላት እጦት መፈታት ያለባቸው የወጣቱ አንገብጋቢ ጥያቄዎች ናቸው፣

ልክ እንደ ኢኮኖሚው ሁሉ የአገራችን ወጣቶች ሰፊ ማህበራዊ ችግሮች አሉባቸው፡፡ በዚህ ዘርፍ ከሚታዩት ቀዳሚ ችግሮች መካከል በህብረተሰብ ደረጃ ለወጣቱ የሚሰጠው ቦታ ዝቅተኛና ምንም ትኩረት የማይደረግበት

መሆኑ ነው:: ወጣቱ የነገው ስርአት ተረካቢ መሆኑን በመገንዘብ ህብረተሰቡም ሆነ እራሱ ወጣቱ ከዚህ እውነታ ጋር የሚመጣጠን ትኩረት ለወጣቱ አይሰጡም:: በመሆኑም ለአካላዊና ለአእምሮአዊ ግንባታው የሚበጁ ስራዎች በሚፈለገው ስፋትና ጥልቀት አይሰሩም:: ወጣቶች በአካል እንዲጎለምሱ፣ በመንፈስ እንዲበስሉና በማንኛውም ሁኔታ ገንቢ ሚና እንዲጫወቱ የሚያደርግ እንቅስቃሴ በሰፊው አይካሄድም::

ወጣቱ በማህበራዊ መስክ ሊሟሉለት ከሚገባቸው ጉዳዮች ዋና ዋናዎቹ በህብረተሰብ ደረጃ በወጣቱ የአሁንና የወደፊት ጥያቄዎችና ጉዳዮች ላይ ብሔራዊ መግባባት መፍጠር፣ ወጣቱ በታቀደና በተደራጀ አኳኋን ችግሮቹን የሚፈታ ብቻ ሳይሆን በህብረተሰቡ ውስጥ ተገቢ ቦታውን እንዲይዝ የሚያደርግ እንቅስቃሴ ማካሄድ፣ በትምህርትና በጤና መስክ ወጣቱ የሚያጋጥሙትን ልዩ ልዩ ችግሮች በመቅረፍ ለወጣቱ የሚበጅ የትምህርትና የጤና ስርአት የመገንባት ወይም በመገንባት ላይ ባለው ስርአት ወጣቱ ተጠቃሚነቱን እንዲያረጋግጥ ማድረግና ለወጣቱ ሰፊና በራሱ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የመዝናኛ አገልግሎትን የማሟላት ጉዳዮች ናቸው:: በነዚህ መስኮች ለአጠቃላይ ህብረተሰቡ ሲባል በሚሰሩ ስራዎች ወጣቱ ተጠቃሚ እንዲሆን የማድረግ ጉዳይ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራበት የሚገባም ሆኗል::

www.abyssinialaw.com

## 1.3 ወጣቱ ተሳትፎውን በሰፊው የሚያረጋግጡ መድረኮች ይሻል፣

ከመልካም አስተዳደር አኳያ በከተማም በገጠርም የሚገኙ ወጣቶች ልዩ ልዩ ችግሮች እንደሚያጋጥሟቸው በጥናት ተረጋግጧል። በዚህ ረገድ ከሚታዩት ችግሮች አንዱ የመገለል ስሜት እንዲያድርባቸው የሚያደርግ የመሳተፊያ መድረክ እጦት ነው። በተካሄደው ጥናት ወጣቶች ሃሳባቸውን ነፃ ሆነው የሚገልፁበት እድል እንዳጡ በምሬት ይገልፃሉ። መንግስትም ሆነ ህብረተሰቡ ለወጣቱ በሚሰጡት አናሳ ትኩረት ምክንያት ወጣቶች በልዩ ልዩ የፖለቲካ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ሃሳብ የሚገልፁበት፣ በእቅድ ዝግጅትና በአፈፃፀም ላይ የሚሳተፉበት መድረክ የላቸውም። በዚህም ምክንያት የአገራችን ወጣቶች ከፍተኛ የመገለል ስሜት አድሮባቸዋል። ከዚህም አለፍ ሲል ወጣቶችን እንደጥፋት ምንጭ አድርጎ የመመልከትና ተገቢ ባልሆነ አኳኋን የመያዝ ችግር ያጋጥማቸዋል። በተጨማሪም ወጣቶችን በአጠቃላይ በህብረተሰብ ጉዳዮች በተለይ ደግሞ በራሳቸው በወጣቶች ጉዳዮች ላይ በሰፊውና በተደራጀ አኳኋን ለማሳተፍ የሚያስችል ስርአት አለመበጀቱ በወጣቶቹ ውስጥ ያለውን የመገለል ስሜት አባብሶታል።

ወጣቶች በርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጥያቄዎች ያሉዋቸው በመሆኑና ለጥያቄያቸውም ከነሱ በላይ ተቆርቋሪ ሊኖር የማይችል በመሆኑ ችግሮቻቸውን በራሳቸው ተሳትፎ ለመለየትም ሆነ መፍትሄ ለማፈላለግ የሚያስችል መድረክ በሰፊውና በቀጣይነት ሊመቻችላቸው ይገባ ነበር። በመንግስትም ሆነ መንግስታዊ ባልሆኑ

ድርጅቶች ፍላጎት ከሚያጠነጥኑ መድረኮች ባሻገር በራሱ በወጣቱ ፍላጎትና ተሳትፎ ላይ የተመሰረቱ መድረኮች በስፋት ማደራጀት ባለመቻሉ ወጣቱ በመገለል ስሜት ተውጧል፡፡ ይህ የመገለል ስሜት ከስራ አጥነትና መሰል የኢኮኖሚ ችግሮች ጋር ተዳምሮ የተስፋ መቁረጥ ዝንባሌን እየፈጠረና እያጎለበተ መሄዱም አልቀረም፡፡

ከፍ ሲል የተገለፁት የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የፖለቲካ ችግሮች በፍጥነት ካልተቀረፉ በወጣቱ ውስጥ ያለውን የመገለልና የተስፋ መቁረጥ አዝማሚያ የማባባስ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በአንፃሩ ችግሮቹ ከተቀረፉ የአገራችን ወጣቶች ከመቼውም ጊዜ በተሻለ ደረጃ በአገር ግንባታ ሂደቱ ውስጥ በንቃትና በተደራጀ አኳኋን ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡ ከላይ በዝርዝር የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ወጣቶች ሁለንተናዊ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው በዚህ ፓኬጅ በዝርዝር ቀርቧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከኢትዮጵያ ወጣቶች መካከል ልዩ ትኩረት የሚሹ ወጣቶች እንዳሉ የሚታወቅ በመሆኑ በዚህ ፓኬጅ ተሣታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ልዩ ትኩረትና ጥረት ማድረግ እንደሚጠይቅ መገንዘብ ይገባል፡፡ የአገራችን የዛሬም ሆነ የነገ እድል የሚወሰነው በወጣቱ ትውልድ ላይ በሚካሄደው ጠቃሚ ኢንቨስትመንት በመሆኑ በጠራ ራእይና ስትራቴጂ ላይ የተመሰረተ ዝርዝር የወጣት እድገት ፓኬጅ መቅረፅ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የኢትዮጵያ ወጣቶች ራእይና ስትራቴጂ፣

## 1. የወጣቶች የልማትና የእድገት ራእዩ፣

ስለወጣቱ የሚኖረን አገራዊ ራእይ በግልፅ ጠርቶ ካልተቀመጠ ወጣቱንም ሆነ መላውን ህብረተሰብ በወጣቱ ጥያቄዎች ዙሪያ በቀጣይነት ማንቀሳቀስ አይቻልም:: በዚህ ረገድ ቀደም ሲል ወጣቱን በተመለከተ የተቀረፁ ልዩ ልዩ ራእዮች የነበሩ ቢሆንም በአንዳንድ ገፅታዎች ላይ ብቻ የሚያተኩሩ በመሆናቸው ሁሉን አቀፍ ባህሪ ያለውና ገላጭ የሆነ አዲስ ራእይ መቅረፅ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል:: በዚህ መሰረት ስለወጣቱ የሚኖረን ራእይ :-

> "ሁለንተናዊ ስብእናው የተሟላ፣ በአገር ግንባታ ሂደት ሰፊ፣ ንቁና የተደራጀ ተሳትፎ ያለውና ተጠቃሚ የሆነ፣ የተጀመረውን የለውዓ ሂደት ተረክቦ የሚያስቀጥል ወጣት ትውልድ ተፈጥሮ ማየት::" የሚል ይሆናል::

## 2. የወጣቱን ጥያቄዎች ለመመለስ የምንከተላቸው ስትራቴጂካዊ አቅጣጫዎች፣

በዚህ ክፍል ትኩረት የተሰጣቸው ዋና ዋና ጉዳዮች የወጣቶችን ችግሮች ለመለየትና ለመቅረፍ ቁልፍና ዘላቂ ሚና የሚጫወቱ ሃይሎችን መለየት፣ እነዚህን ሃይሎች በአግባቡ የመገንባትና ለወጣቱ ጥያቄዎች መልስ በሚያስገኝ አኳኋን የማሰማራት ጉዳዮች ናቸው:: በዚህ መሰረት

የወጣቱን ጥያቄዎች ለመመለስ፣ ተሳትፎና ተጠቃሚነቱን ለማረጋገጥና ወጣቱን ለታሪካዊ ሃላፊነቱ ለማብቃት የሚከተሉትን ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎች መከተል፡፡

## 2.1. ወጣቱን ዋነኛ ኃይል አድርጎ መረባረብ፣

የወጣቱን ችግሮች ለመለየትና ለመቅረፍ የሚካሄድ ጥረት ራሱን ወጣቱን ዋነኛ ሃይል አድርጎ ከማንቀሳቀስ ውጭ ሊታሰብ የሚችል አይደለም፡፡ በዚህ ረገድ በራሱ በወጣቱም ሆነ በህብረተሰቡ ውስጥ ስር ሰደው የቆዩ የተዛቡ አመለካከቶች አሉ፡፡ ከነዚህም ዋነኛው የወጣቱን ችግር በመንግስት ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ትከሻ ላይ ጥሎ ወጣቱን ሚና አልባ የማድረግ አዝማሚያ ነው፡፡ ወጣቱ ያሉበት ችግሮች ተቀርፈው ራእያችን እውን ይሆን ዘንድ የሚከተሉትን ወጣቱን ዋነኛ ኃይል የሚያደርጉ ስትራቴጂዎችን እንከተላለን፡፡

### 2.1.1. ወጣቱን ዋነኛ ችግር ፈች ኃይል እንደሆነ ተገንዝቦ እንዲንቀሳቀስ ማስቻል፣

- ወጣቱ የራሱን ችግሮች ለመፍታት በቅድሚያና በወሳኝነት መሰለፍ ያለበት እራሱ እንደሆነ በተሟላ አኳኋን እንዲገነዘብ የማድረግ ስራ መስራት፣
- ወጣቱ ዋነኛ ችግር ፈች ሃይልነቱን እንዳይገነዘብ የሚያደርጉ አዝማሚያዎችን በቀጣይነት በመታገል

የማስተካከልና የወጣቱን በራስ የመተማመን አቋም የማጠናከር አቅጣጫ እንከተላለን፡፡

### 2.1.2. ወጣቱን ዋነኛ ችግር ፈችነቱን በተግባር እንዲያረጋግጥ የሚያስችሉ የተሳትፎ መድረኮች እንዲመቻቹለት ማድረግ፣

- ወጣቱ ችግር ፈቺ ሊሆን የሚችለው ችግሮችን በመለየት ላይም ሆነ ለችግሮች መፍትሄ በማፈላለግ እንዲሁም የተቀየሱትን መፍትሄዎች በተግባር ለማዋል የሚችልባቸውን የምክክርና የተግባር መድረኮች በቀጣይነት መክፈት፣
- ወጣቱ መድረክ እንዳይኖረው ወይም በተከፈቱ መድረኮች በብቃት እንዳይጠቀም የሚያደርጉ ዝንባሌዎችን እየለዩ በማያቋርጥ ሁኔታ በራሱ በወጣቱ ወሳኝ ተሳትፎ መፍታት፣
- የመድረኮቹ አይነትና ባህሪ ለወጣቱ ተስማሚ መሆናቸውን ማረጋገጥና ወጣቱ በመድረኮቹ አይነትና ባህሪ አወሳሰን ላይ ወሳኝ ሚና እንዲጫወት ማድረግ፣

### 2.1.3. የወጣቱን ተሳትፎ በብቃት ለማረጋገጥ የትምህርት፣ የሞያ ክህሎትና የአመራር ብቃት የማሳደግ ስራዎችን መስራት፣

- ወጣቱ በመድረኮች ተጠቅሞ በብቃት እንዲሳተፍ እንዲሁም በልዩ ልዩ ማህበረሰባዊ ክንዋኔዎች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል የትምህርትና የስልጠና እድል እንዲስፋፋ ማድረግ፣
- ወጣቱ ከወዲሁ የአመራር ልምዱ እየሰፋ ብቃቱም እየጨመረ እንዲሄድ የአመራር አቅም ግንባታ ስርአት ቀርፆ ተግባራዊ ማድረግና ሰፊ የአመራር ሃይል ለማፍራት የሚያስችል እንቅስቃሴ ማካሄድ፣
- ወጣቱ የራሱን የአመራር አቅም በሰፊው በመገንባት አስፈላጊነት ላይ የተሟላ ግንዛቤ ይዞ ከሱ የሚጠበቀውን ሁሉ እንዲያሟላ ማድረግ፣ ከዚህ በተጨማሪ የወጣቱን የአመራር አቅም ግንባታ የሚያደናቅፉ ችግሮችን እየተከታተሉ መፍታትና ምቹ ሁኔታውን ማጐልበት፣

### 2.1.4. ወጣቱ በየስራ መስኩና በየፍላጐቱ ዙሪያ እንዲደራጅና ለወጣቱ የጋራ ጥያቄዎች ደግሞ የጋራ አደረጃጀቶች እንዲጐለብቱ ማድረግ፣

- ወጣቱ ከላይ የተጠቀሱትን ስትራቴጂዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚችለው በነፃና ፍላጐቱን በሚወክሉ ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች ሲሰባሰብ እንዲሁም የጋራ የወጣትነት ፍላጐቱን በተጠናከረ አኳኋን ለማራመድ የሚያስችለው አገራዊና ክልላዊ የወጣት አደረጃጀት ሲፈጥር እንደሆነ እንዲገነዘብ ማድረግ፣
- በዚህ መሰረት የወጣቱን ልዩ ልዩ ፍላጐቶች ለማርካት ልዩ ልዩ የወጣት አደረጃጀቶች እንዲፈጠሩ ማበረታታትና ሁሉንም በእኩልነት ተመልክቶ መደገፍ፣
- ወጣቱ በየራሱ ልዩ ልዩ ፍላጐቶች ዙሪያ ልዩ ልዩ ማህበራት መመስረቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ማህበራቱ በተናጠል ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ በተጨማሪ በጋራ የወጣቱን ጥያቄዎች እንዲያራምዱ እድል የሚሰጥ አገራዊ የወጣቶች ፌዴሬሽን እንዲመሰረት ማድረግ፣ ፌዴሬሽኑ ልዩ ልዩ የወጣት ማህበራት ተሰባስበው የሚመሰርቱት እንዲሆን ማድረግ፣
- በወጣቶች ጥያቄ ላይ ለብዙሃኑ ወጣት የሚጠቅም ሃሳብ የሚያፈልቁትንና በተግባርም ታግለው ወጣቱን በማታገል ብቁነታቸውን ያረጋገጡት የግንባር ቀደምነት ሚናቸውን እንዲጫወቱ ተገቢውን ትኩረት መስጠት፣

### 2.1.5. ወጣቱ የተቀመጡትን ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ለማድረግ ግንባር ቀደም ተዋናይና የሂደቱ ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያደርግ አቅጣጫ መከተል፣

- ወጣቱ ተሳታፊነቱንና ተጠቃሚነቱን ሊረጋገጥ የሚችለው ከላይ የተዘረዘሩት ስትራቴጂዎችና ቀጥለን የምንዘረዝራቸው ዋና ዋና ተግባራት በስራ ላይ ሲውሉ እንደሆነ በማመን ለስትራቴጂና ዝርዝር ተግባራቱ በስራ ላይ መዋል ወጣቱን ዋነኛ ተዋናይ እያደረገ ቀጣይ እንቅስቃሴ ማካሄድ፣
- ወጣቱ የሚሳተፍና የሚጠቀምባቸውን ፕሮግራሞች የመቅረፅና እነዚህንም በራሱና በሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ትብብር ለማስፈፀም የሚያስችል ዝርዝር እቅድ እያዘጋጁ የመፈፀም ልምድና ባህል እንዲያዳብር ማድረግ፣
- ወጣቱ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ላይ የሚያጋጥሙትን መሰናክሎች በፅናት ተቋቁሞ እንዲፈታ በትኩረት መንቀሳቀስ፣ እንዲሁም ከእያንዳንዱ ተግባራዊ እንቅስቃሴው የሚወስዳቸውን ትምህርቶች በተሟላ አኳኋን የሚወስድና ቀጣዩን ተግባራዊ እንቅስቃሴ

የሚያጐለብትበት የልምድ መቀመርና ማስተላለፍ ስርአትን ማጠናከር፣

- በየመስኩ ለወጣቱ የተፈጠሩትን መልካም አጋጣሚዎች እንዴት እየተጠቀምንባቸው እንደሆነና ምን ውጤት እንደተገኘ ከወጣቱ ጋር በየጊዜው በመገምገም የበለጡና ከፍተኛ ለውጥ የሚያመጡ አሰራሮችን በቀጣይነት ጥቅም ላይ ማዋል ዋና ዋና ስትራቴጂዎቻችን ይሆናሉ:: እነዚህ ስትራቴጂዎች የወጣቱን ጥያቄና ችግሮች ዋነኛ መላሽ ሃይል ነው ብለን የምንተማመንበትን ወጣቱን ለመገንባትና አደራጅቶ በማንቀሳቀስ ተሳትፎውንና ተጠቃሚነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ እንደሆኑ ይታመናል::

## 2.2. መንግስት የመደገፍ ሚናውን በብቃት እንዲወጣ ማድረግ፣

- ከወጣቱ በመቀጠል የወጣቱን ጥያቄዎች ለመመለስ ቁልፍ ደጋፊ ሚና የሚጫወቱ ዋነኛ ደጋፊ ሃይሎች አሉ:: እነዚህን መለየትና ሚናቸውን በብቃት እንዲወጡ ማድረግ ለወጣቱ ጥያቄዎች መመለስ ከፍተኛ ተፈላጊነት አለው:: በዚህ ረገድ ዋነኛ ደጋፊ ሃይሎች ተብለው ከሚወሰዱት መካከል መንግስት በቀዳሚነት ይጠቀሳል:: በመሆኑም ስለወጣቱ ያለንን ራእይ እውን ለማድረግ መንግስት ሊጫወተው የሚችለውንና

የሚገባውን ሚና ለይቶ መረባረብ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መሰረት መንግስት፣

- የወጣቱን ተሳትፎ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ልዩ ልዩ መድረኮች እንዲከፈቱ፣ በመንግስት አካላት በኩል ለወጣቶች የሚሆኑ መድረኮችን በስፋት የመክፈትና የተሳትፎ እድልን የማስፋት አመለካከት እንዲዳብር ማድረግ፣
- ወጣቱ በህብረተሰቡ ውስጥ ተገቢ ሚናውን እንዲጫወትም ሆነ የራሱን የወጣቱን ጥያቄዎች በራሱ ዋነኛ ኃይልነት እንዲመልስ ለማድረግ የሚያስችል ሰፊ የአመራር አቅም እንዲገነባ መንግስት የበኩሉን ሚና እንዲጫወት ማድረግ፣ በዚህ ረገድ የስልጠናና የአቅም ግንባታ ተቋማትን የመክፈት ጥረቱ ተጠናክሮ እንዲቀጥልና ወጣቱም በነዚህ ተቋማት ተጠቃሚ እንዲሆን ሁኔታውን ማመቻቸት፣
- በአገር አቀፍ ደረጃ የተነደፈውን የልማት፣ የሰላምና የዴሞክራሲ ስትራቴጂን መላውን ህብረተሰብ አንቀሳቅሶ ተግባራዊ ማድረግ፣ በዚህ ሂደት ወጣቱ ተሳታፊና እኩል ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሁኔታ ማመቻቸት መንግስት ለወጣቱ ፓኬጅ ተግባራዊነት ሊጫወት ከሚገባቸው ሚናዎች ዋና ዋናዎቹ ሆነው ይገኛሉ፡፡

# ያአል ሦስት

## የገጠር ወጣቶችን እድገትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፣

## I. የገጠሩን ወጣት ጥያቄዎች መመለስ፣

### 1.1. የገጠሩን ወጣት የኢኮኖሚ ጥያቄዎች መመለስ፣

አላማ፣

1. በአገራችን የተፋጠነና ህዝብን ተጠቃሚ የሚያደርግ ልማት እውን ለማድረግ የተነደፈውን ፖሊሲና ስትራቴጂ በመላው ህዝብ ተሳትፎ ተግባራዊ ማድረግ፤
2. ወጣቱ አገራዊውን የልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ ተግባራዊ ለማድረግ ቁልፍ ተዋናይ እንዲሆንና በጥረቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ፣

#### 1.1.1. የገጠሩን ወጣት የመሬት ጥያቄ መመለስ፣

ሀ) ወጣቱ በቤተሰቦቹ መሬት ላይ በሚካሄደው ልማት ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ፣

- በወላጆች እጅ ያለን መሬት በመበጣጠስ የምርት ጭማሪን ማረጋገጥ እንደማይቻል በአንፃሩ ደግሞ ባለው መሬት የሁሉንም ጉልበት አዋህዶ በማንቀሳቀስ መጠቀም ከተቻለ ከፍተኛ የምርት ጭማሪ በአጭር ጊዜ ማምጣትና

መላውን ቤተሰብ መጥቀም እንደሚቻል የጋራ ግንዛቤ ማስያዝ፣

- በገጠር ልማት ስትራቴጂያችን መሰረት በቤተሰብ መሬት ላይ የሚካሄደውን ልማት ማጧጧፍ፣ እያንዳንዱ ቤተሰብ ከተቻለ ሁለቴና ሶስቴ ካልሆነም በአንድ የምርት ወቅት ከፍተኛ ምርት ለማግኘት በሚያስችል መልክ መሬቱን እንዲያለማ ማድረግ፣
- በቤተሰብ መሬት ላይ የሚካሄደው ልማት ለስራ የደረሱ የቤተሰቡን አባላት ጉልበት አሟጦ በመጠቀም ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ፣ ወጣቶች በዚህ ረገድ ከፍተኛ ሃላፊነት እንዳለባቸው እንዲገነዘቡ ማድረግ፣ ወጣት ተኮር የሆኑ የተሻሻለ የጉልበት አጠቃቀም ቴክኖሎጅዎችን በማስተዋወቅና በማሰልጠን እንዲሁም ጉልበቱን በውጤታማነት በማሰማራት የምርት ጭማሪ ማምጣት፣
- የመሬቱን ምርታማነት እንደሚያሳድጉ በሚታመንባቸው የጥቁር አፈር እርሻ፣ የመስኖና የውሃ ማቆር ስራዎች፣ እንዲሁም ለእርጥበትና እርጥበት አጠር አካባቢዎች ተስማሚ ሆነው የተቀየሱ የግብርና ልማት ስልቶችን ሁሉም ለስራ የደረሱ የቤተሰቡ አባላት እንዲያውቁዋቸው የሚያደርግ ስልጠና በተከታታይ መስጠትና በተግባር ማዋል፣

- በቤተሰብ ማሳ ላይ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም ገንዘብ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለወጣቱ ወይም ለቤተሰቡ በጋራ የብድር አቅርቦት ማመቻቸት፣
- በቤተሰብ የጋራ ጉልበት የሚገኘውን የምርት ጭማሪ በፍትሃዊ መንገድ በጋራ የሚጠቀሙበት ስርአት ማበጀት፣ በዚህ መሰረት ወደስራ ከመግባታቸው በፊት በሚገኘው የምርት ጭማሪ የቤተሰቡን የጋራ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ስምምነት በሁሉም የቤተሰቡ አባላት ተሳትፎ መፍጠር፣
- ወላጆች ወጣት ልጆቻቸው ቤተሰብ የመመስረት፣ ጎጆ የመውጣትና የመቋቋም ህልም እንዳላቸው ተገንዝበው ለልጆቻቸው የተመቻቸ ሁኔታ ለመፍጠር እንዲተጉ፣ ወጣቶችም የወላጆቻቸው አቅም እየደከመ እንደሚሄድ ተገንዝበው በመተሳሰብ ሊረዳዱ እንደሚገባቸው የጋራ ግንዛቤ መፍጠር፣

## ለ) በየቀበሌው ሊታረሱ የሚችሉና በማንም ያልተያዙ የእርሻ መሬቶችን ለወጣቱ ማከፋፈል

- በየቀበሌው በተለይም ብዙ ህዝብ ባልሰፈረባቸው ቆላማ አካባቢዎች በማንም ያልተያዘውን መሬት ለቀበሌው ወጣት ማከፋፈል፣

- በተለያዩ ምክንያቶች መሬታቸውን የለቀቁ ሰዎች ሲኖሩና እስካሁን ወራሽ ሳይኖራቸው በሞት የተለዩ ገበሬዎችን መሬት ከቀበሌ አስተዳደር እጅ አውጥቶ ለወጣቱ ማከፋፈል፣ መሬት የመለየቱ ስራ በወጣቱ ተሳትፎ ማካሄድ፣
- በአንዳንድ ወረዳዎች በአስተዳደር እጅ የሚገኘውን መሬት ለወጣቶች በተናጠል ወይም በጋራ መጠቀሚያ አድርጐ መስጠት፣
- የመሬት ክፍፍሉ በግልፅና በፍትሃዊ መመሪያ የሚከናወን እንዲሆን ማድረግ፣ በዚህም ትዳር ለመሰረቱና ምንም መሬት ለሌላቸው ቅድሚያ መስጠት፣ ትዳር ላልመሰረቱ ወጣቶችም በቅደም ተከተል መስጠት፣
- ወጣት ሴቶች በመሬት አደላው ውስጥ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- ወጣቶቹ ባገኙት መሬት ላይ ከፍተኛ ዋጋ የሚያስገኙ ምርቶችን እንዲያመርቱ በስልጠናና በአቅርቦት መደገፍ፣

ሐ) የተራራ መሬትን ለወጣቱ ማከፋፈል፣ ተራሮችን አልምቶ እንዲጠቀም በስልጠና፣ በማቴርያል አቅርቦትና የብድር አገልግሎት በመስጠት ማገዝ፣

- በማንም ያልተያዙ ተራራማ መሬቶችን ለይቶ ለወጣቱ ማከፋፈል፣ ወጣቱ በተናጠል ወይም በራሱ ፈቃደኝነት ተደራጅቶ ተራሮችን እንዲያለማ ማድረግ፣

- በተራሮች ላይ የሚካሄደው ልማት አግሮ ፎሬስትሪና የእንስሳት ሃብት ልማትን አዋህዶ በማካሄድ የሚፈፀም እንዲሆን ማድረግ፣
- አግሮ ፎሬስትሪ ረዘም ያሉ አመታትን የሚጠይቅ ሊሆን ስለሚችል ወጣቱ ጊዜያዊ ጥቅሞችን የሚያገኝባቸውን ተጨማሪ ስልቶች ጥቅም ላይ ማዋል፣
- በየአካባቢው በቀበሌ አስተዳደር እጅ የሚገኙ ሰው ሰራሽና ከመርሻል ዋጋ ያላቸው ደኖችን ለወጣቱ በመጠቀሚያነት ማከፋፈል፣ የሰው ሰራሽ ደኖች አጠቃቀም ስርአቱ ወጣቶች አዲስና የላቀ ቁጥር ያለው ደን ከማልማታቸው ጋር ተመጋጋቢ እንዲሆን ማድረግ፣ ባለው የመጠቀም ብቻ ሳይሆን የተጠቀመበትን ይበልጥ የመተካት አመለካከትና ተግባር የሚያዳብር ስርአት ማበጀት፣
- በተራሮች ላይ ልማት ለማካሄድ የቆረጡ ወጣቶች በአጭር ጊዜ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ በማረጋገጥ በመስኩ ልማት ሊካሄድ አይችልም የሚለውን አመለካከት መስበር፣
- ተራሮችን ለማልማትና ለመጠቀም ዝግጁ ለሆኑ ወጣቶች የዘር ጥያቄ በማሟላት የሙያ ስልጠና በመስጠትና የብድር አቅርቦት ወዘተ በማቅረብ መደገፍ፣
- በቀበሌና በወረዳ አመራር ደረጃ በተራሮች ልማት ጥያቄ ላይ የተሟላ ግልፅነት መፍጠር፣ በተለይም በተራራማ

አካባቢዎች የተራራ ልማት የስራችን አይነተኛ ገፅታ እንዲሆን ማድረግ፣

መ) በክልል ውስጥ ለሰፈራ ምቹ በሆኑ አካባቢዎች ወጣቶችን ማስፈር፣

- ሰፈራ የማካሄድ እቅድ ያላቸው ክልሎች ወጣቱን የሰፈራ ፕሮግራሙ ዋነኛ ተጠቃሚ ማድረግ፣
- ለሰፈራ በሚካሄደው ምልመላ ለወጣቱ ትኩረት መሰጠቱን ማረጋገጥ፣ ወጣቱ የሰፈራ ፕሮግራምን ጠቃሚነት እንዲገነዘብ ማድረግና ማደፋፈር፣
- ሰፈራ ለሚሄድ ወጣት መሬት መሰጠቱን ማረጋገጥ፣ ሰፋሪው ወጣት በአጭር ጊዜ ከራሱ አልፎ ለገበያ የሚያመርትና የሚጠቀም እንዲሆን በስልጠና፣ በማቴርያልና በብድር አቅርቦት መደገፍ፣
- ለሰፋሪዎች በሙሉ ተብሎ በሚሰራው የመሰረተ ልማት ማስፋፋት ስራ ወጣቱም ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ፣
- በሰፋሪ ተቀባይ አካባቢዎች የሚኖረውን ህብረተሰብ ለወጣቱ አመች ሁኔታ በመፍጠር ጉዳይ ላይ የጋራ ግንዛቤ እንዲያዳብር ማድረግ፣

### 1.1.2 ከግብርና ውጭ ላሉ የገጠር ልማት ስራዎች ልዩ ትኩረት በመስጠት የወጣቱን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣

መንግስት የአገራችንን ልማት ለማፋጠን በተለይ በገጠሩ ትኩረት ከሰጣቸው ጉዳዮች አንዱ ከግብርና ውጭ ያሉ የስራ መስኮች እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ አርሶ አደሩም በዚህ ሂደት ዋነኛው ተዋናይና ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ ነው:: ይህን የመንግስት የትኩረት አቅጣጫ ተከትሎ በመጓዝና ተግባራዊ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት ወጣቱ ንቁ ተዋናይና እኩል ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ይገባል:: በዚህ መሰረት:-

**ሀ) በከተሞች በፍጥነት በማደግ ላይ ላለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የሚሆን ጥሬ እቃ የማቅረብ እንቅስቃሴ እንዲስፋፋና በዚህም ወጣቱ እንዲሳተፍበትና ተጠቃሚነቱም እንዲረጋገጥ ማድረግ፣**

- በከተማው የሚካሄደውን ኮንስትራክሽን በገጠር ካሉ የጥሬ እቃ ምንጮች ጋር አያይዞ ለወጣቶች የስራ እድል መፍጠሪያ አድርጎ ለመጠቀም አስፈላጊ ሆነው የተገኙ የመሰረተ ልማት በተለይም የመንገድ ስራዎች መስራት፣

- በነዚህ የስራ መስኮች የሚሰማሩ ወጣቶችን በማህበር አደራጅቶ ማንቀሳቀስ፣ ድርጅታቸው ዴሞክራሲያዊና የሁሉንም አባላቱን ጥቅም የሚያስጠብቅ እንዲሆን ማድረግ፣

**ለ) በገጠር በሚካሄዱ ግንባታዎች ወጣቱን ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ፣**

- ወጣቱ በገጠር በሚካሄዱ ልዩ ልዩ የኮንስትራክሽን ስራዎች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን ከፊሉን በልዩ ልዩ ሞያዎች ማሰልጠን፣
- በህዝብ ተሳትፎ በሚሰሩ ስራዎች ላይ የሞያተኛ ስምሪት የሚፈልጉትን ስራዎችን በመለየት እና በመንግስት ገንዘብ ብቻ የሚሰሩ የኮንስትራክሽን ስራዎችን ሰልጥነው ለተደራጁ ወጣቶች መስጠት፣
- በነዚህ መስኮች ለሚሰማሩ ወጣቶች የብድር አገልግሎት ማቅረብ፣ በተጨማሪም የእጅ መሳሪያዎች በዱቤ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

**ሐ) ልዩ ልዩ የእደ ጥበብ ስራዎችን በማስፋፋት ወጣቱን ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ፣**

- መንግስት የነደፈውን የእደ ጥበብ ስራዎችን የማስፋፋት ስትራቴጂ ተግባራዊ ማድረግና

ወጣቶች በዚህ ሂደት ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣

- ወጣቶች የእደ ጥበብ ምርቶችን የማምረት ችሎታቸው እንዲዳብር ልዩ ልዩ ስልጠናዎች ማዘጋጀትና ወጣቶች አንዲሳተፉባቸው ማድረግ፣
- የሙያና ስልጠና ትምህርት ማእከላት በነዚህ መስኮች የሰለጠነና ብቁ የሰው ሃይል በማፍራት በመስኩ ለሚካሄደው እንቅስቃሴ አመች ሁኔታ እንዲፈጥሩ ማብቃት፣
- የእደ ጥበብ ስራዎች ላይ ለሚሰማሩ ወጣቶች አስፈላጊውን የብድር አቅርቦት ማሟላት፣ ለምርቶቻቸው የመሸጫ ቦታዎችን ማመቻቸት፣ የጥሬ እቃ አቅርቦትን በተደራጀ ሁኔታ ለማሟላት መንቀሳቀስ፣
- ወጣቶቹ በህብረት ስራ ማህበራት ተደራጅተው ለተሻለ እድገት እንዲበቁ ማድረግ፣

መ) የገጠር ወጣቶች በአነስተኛ የንግድ ስራዎች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣

- ለከተሞች የሚቀርቡ ልዩ ልዩ ምርቶችንና አገልግሎቶችን፣ እንዲሁም እዚያው ለገጠሩ ማህበረሰብ የሚቀርቡ ልዩ ልዩ ምርትና አገልግሎቶችን እንዲያቀርቡ ማድረግ፣

- በዚህ መስክ ወጣቶች በአነስተኛ ንግድ ስራዎች ላይ ያሉ እድሎችን የሚያውቁበት፣ በእድሎቹ ለመጠቀም የሚያስችላቸው ስልጠናና የብድር አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ ማመቻቸት፣

ሠ) ሌሎች ወጣቱ የሚለያቸው ከግብርና ውጭ ያሉ የስራ መስኮችን ማስፋፋት፣

- ወጣቱ ከተዘረዘሩት ውጭና በተዘረዘሩትም ውስጥ ሊጨመሩ ይገባቸዋል የሚላቸውን እንዲያቀርብ ማድረግና ሊደግፉ የሚገባቸውን ሁሉ መደገፍ፣

## 1.1.3. በገጠር ብድር ስርአቱ ውስጥ ለወጣቱ የሚሆን የተለየ ስርአት ማበጀት፣

- በየክልሉ የገጠር ብድር ተቋማትን በፋይናንስ አቅም፣ በአሰራርና በአደረጃጀት ማጠናከርና በዚህም ውስጥ ወጣቱ የኢኮኖሚ ጥረቶች ድጋፍ የሚሰጥ የብድር ስርአት ማመቻቸት፣
- በብድር አሰጣጥ ስርአቱ ውስጥ የሚታዩ ችግሮችን በቀጣይነት እየተከታተሉ መፍታትና የወጣቱን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣

- ወጣቶች ከፋይናንስ ተቋማት በሚያገኙት ብድር ውጤታማ ስራ እንዲሰሩ የሚያስችል የአመለካከትና የሙያ ብቃት እንዲያዳብሩ ማስቻል፣
- በብድር በአግባቡ የመጠቀም ብቻ ሳይሆን ብድር የመመለስ ባህል እንዲጠናከር ማድረግ፣

### 1.1.4 ወጣቶችን ብቁ የኢኮኖሚ ተዋናይ ለማድረግ የሚያስችል የሙያና ክህሎት ስልጠና መስጠት፣

- በትምህርት ገበታ ላሉ ወጣቶች ከ4ኛ ና 8ኛ ክፍል ማጠናቀቅ በኋላ በግብርናና ከግብርና ውጭ ባሉ የስራ መስኮች ላይ ቀጣይ ስልጠናዎች የሚሰጥበት ስርአት ማበጀት፣
- በየትምህርት ቤቱና በገበሬዎች ማሰልጠኛ ተቋማት አማካይነት የሚካሄደውን ስልጠና የሚመሩ ብቁ አሰልጣኞች ማዘጋጀትና ወይም ያሉትን የአመለካከት ለውጥ እንዲያመጡና በሙያም እንዲዳብሩ በማድረግ መመደብ፣
- የሚሰጠውን ስልጠና ካሪኩለም ይዘት በወጣቶቹ ፍላጐት መሰረት ማዘጋጀት፣
- በመደበኛ ትምህርት ቤቶች በሚካሄደው ስልጠና የሚሳተፉ ወጣቶችን በአመለካከት በሙያ ችሎታ መገንባት፣ የስራ ፈጣሪነትን አስተሳሰብ ማዳበር፣

### 1.1.5 ወጣቱ ለሚያመርታቸው ምርቶችና ለግብአት ፍላጐቱ የሚሆን ገበያ ማመቻቸት፣

- ወጣቶች በህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ በፈቃደኝነት አባል እንዲሆኑ ማበረታታት፣
- በመንግስትና በግሉ ሴክተር፣ በከተማና በገጠር ተፈላጊነት ያላቸውን ምርቶች ህብረተሰቡ በፍጥነት እንዲገነዘብ ለማድረግ በሚገነባው የመረጃ ስርአት አማካይነት ለወጣቱም መረጃ ማስተላለፍ፣
- የሚፈጠሩ አዳዲስ የገበያ እድሎችን ከማስተዋወቅ በተጨማሪ ባሉትም የተሻለ እድል የሚያገኙበት መንገድ ማመቻቸት፣

## 1.2. የገጠሩን ወጣት የማህበራዊ ጥያቄዎች መመለስ፣

**አላማ፣**

1. በገጠር የተሟላ ማህበራዊ ለውጥ እንዲመጣ መንግስት የነደፋቸው ፕሮግራሞች ተፈፃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣የገጠር ማህበራዊ ችግሮችን ለመፍታት በሚካሄደው እንቅስቃሴ ወጣቱ ንቁ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ፣
2. የወጣቱን ማህበራዊ ችግሮች በራሱ ሰፊና ንቁ ተሳትፎ በተቻለ ፍጥነት በመቅረፍ ወጣቱ በአካልና በአእምሮ እንዲዳብርና በአገር ግንባታ ረገድ መጫወት ያለበትን ሚና በመጫወት ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ፣

### 3.2.1. የወጣቱን የትምህርትና ስልጠና ፍላጐት ማሟላት፣

#### ሀ) የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን በጥራት በማስፋፋት የወጣቱን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣

- የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ በማያቋርጥ ሁኔታ እንዲያድግና አብዛኛው የገጠሩ ወጣት 8ኛ ክፍልን እንዲያጠናቅቅ፣ በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤት የማምጣት ብቃት ያላቸው ደግሞ ወደሁለተኛ ደረጃና ወደ ከፍተኛ ትምህርት የሚሸጋገሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- በገጠር የሚሰጠው ትምህርት ጥራቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ፣ የገጠሩ ወጣት በቀለም ትምህርትና በሞያ እንዲሁም በስነ ምግባርና ስነ ዜጋ እሴቶች የዳበረ እንዲሆን ማድረግ፣
- በገጠር በተለያዩ ምክንያቶች ከ4ኛ ክፍል በላይ መሄድ ያልቻሉ ወጣቶች የሚኖሩ ከሆነ ደረጃውን የጠበቀ የሞያ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣ በተመሳሳይ መልኩ 8ኛ ክፍል ላጠናቀቁ የገጠር ወጣቶች በአርሶ አደሮች ማሰልጠኛ ማእከላት አማካይነት በግብርናና ከግብርና ውጭ ባሉ መስኮች ስልጠናዎችን መስጠት፣
- ትምህርት ቤቶች ለወጣቱ ስልጠና የሚበጁ ልዩ ልዩ ማቴሪያሎችን እንዲያሟሉ ማድረግ፣ ትምህርት ቤቶች ለወጣት ወንዶችና ወጣት ሴቶች ማሟላት ያለባቸውን የተለያዩ አገልግሎቶች እንዲያሟሉ ጥረት ማድረግ፣

- መምህራንና ህብረተሰቡ ለወጣቶች የትምህርትና የስልጠና ፍላጐት ቅድሚያ በመስጠት በሚቻላቸው ሁሉ ጥራቱን ለመጠበቅና ለማስፋፋት የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ፣
- ትምህርት ቤቶች የወጣቱን አካላዊና አእምሮአዊ ግንባታ ለማጠናከር በተለይ ደግሞ በአስተሳሰብ ደረጃ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ዴሞክራሲያዊ የሆነ የውስጥ አስተዳደር እንዲያዳብሩ ማድረግ፣

**ለ) የትምህርት እድል ላላገኙ ወጣቶች የትምህርት እድል ማመቻቸት፣**

- በገጠር ያልተማሩ ወጣቶች የትምህርት እድል በተለይ የመሰረተ ትምህርትን በማስፋፋት የተወሰነ የመማር እድል እንዲያገኙ ማድረግ፣ ያልተማሩ የገጠር ወጣቶችን ለማስተማር ጥቅም ላይ የዋሉ መልካም ልምዶችን ቀምሮ ለወጣቶች ማቅረብና ከተስማሙበት ተግባራዊ ማድረግ፣ ለዚህ ትምህርት መስፋፋት አስፈላጊ የሆነውን ባጀት መመደብ፣ ለትምህርቱ የሚበጁ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን አሟልቶ ማቅረብና በራሳቸው በወጣቶቹ ተሳትፎ የሚተዳደርበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- በገጠር መሰረተ ትምህርትን ለማስፋፋት የሚችሉ አካላትን ሁሉ በዚህ ስርአት አሰልጥኖ በመደበኛ መንገድ ማሰማራት፣

**ሐ) ላልተማሩ ወጣቶች ተስማሚ የሙያ ስልጠና መርሃ ግብር ቀርፆ ተግባራዊ ማድረግ፣**

- በገጠር ያልተማሩ ወጣቶች ከመሰረተ ትምህርት ጐን ለጐን የሙያ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣ የሙያ ስልጠናው በወጣቶቹ ፍላጐት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ፣ መንግስት ስልጠና ሊሰጥባቸው ይገባቸዋል የሚላቸውን መስኮች ለይቶ ለወጣቶች በማቅረብ ወጣቱ ከቀረበለት የስልጠና እድል መካከል በመረጠው መስክ እንዲሳተፍ እድል መስጠት፣
- ለስልጠናው የሚያስፈልጉ መምህራንን ማዘጋጀት፣ አስፈላጊ ቁሳቁሶችን ማቅረብና ከገጠር የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት ጋር በተጣመረ አኳኋን ስልጠናውን ተግባራዊ ማድረግ፣
- ይህን ስራ በተፋጠነ ሁኔታ ማከናወን ይቻል ዘንድ በገጠር በየቀበሌው የሚገኘውን ያልተማረ ወጣት መለየትና መዝግቦ መያዝ፣ ለስልጠና ፈቃደኛ የሚሆኑበትን ስልት ቀይሶ ተግባራዊ ማድረግ፣

**መ) የገጠሩ ወጣት የሁለተኛና የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎው እንዲጨምር ማድረግና በዚህ ረገድ የሚያጋጥሙትን ችግሮች መፍታት፣**

- በገጠር የሚገኙ ወጣት ተማሪዎች በትምህርታቸው ጐብዘው ለሁለተኛ ደረጃ ከዛም አልፎ ለከፍተኛ ትምህርት የሚበቁ ተማሪዎች ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ እንዲሄድ ማድረግ፣ ከዚህ በመነሳት የተማሪዎችን የትምህርት ብቃት የሚጨምሩ የትምህርት ጥራትና የቱቶሪያል አገልግሎት እንዲስፋፋ ማድረግ፣
- በችግር ምክንያት ትምህርታቸውን የሚያቋርጡ ወጣቶች በተለይ ደግሞ ሴት ወጣት ተማሪዎች ያሉባቸውን ችግሮች በመፍታት ትምህርታቸውን ለመቀጠል እንዲችሉ ማድረግ፣

## 1.2.2. በመከላከልና በመሰረተ ጤና ላይ ያተኮረ የገጠር ጤና አገልግሎት በማስፋፋት ወጣቱ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ፣

- ወጣቱ በሽታን የመከላከል እውቀቱና ግንዛቤው እንዲያድግ በማድረግ ለልዩ ልዩ በሽታዎች ያለውን ተጋላጭነት መቀነስ፣ በመሆኑም ወጣቱን በሚያጠቁት ልዩ ልዩ በሽታዎች መንስኤና መፍትሄ ላይ ወጣቱ ተወያይቶ የተሟላ ግንዛቤ እንዲይዝ ማድረግና በተግባር መተርጐም፣
- በዚህ መሰረት ወጣቱ ኤች አይቪ ኤድስን፣ ወባና ሌሎች ተዛማጅ በሽታዎች የሚስፋፉበትን መንገድ እንዲያውቅና ይህንንም መከላከል የሚቻልበትን ስርአት ተገንዝቦ በተግባር እንዲያውለው ማድረግ፣ በበሽታ የተጐዱ ወገኖቹን

ለመንከባከብ የሚያስችል ማህበራዊ ሁኔታ እንዲፈጠር ማድረግ፣ በገጠር የኤች አይቪ ኤድስ ምርመራ ማካሄጃ ተቋማትን በማስፋፋት ወጣቱ በነፃ አገልግሎቱን የሚያገኝበት ሁኔታ ማመቻቸት፣

- ወጣቱ በስነ ተዋልዶ ጤና ላይ ያለው ግንዛቤ እንዲያድግና በዚህ መስክ ከሱ የሚጠበቀውን ሚና አውቆ እንዲንቀሳቀስ ማድረግ፣ የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርትን በየደረጃው በመስጠት ወጣቱ ለራሱና ለቤተሰቡ የተመቸ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ እንዲፈጥር ማድረግ፣

### 1.2.3 በወጣቱ ፍላጐትና ተሳትፎ ላይ የተመሰረቱ ልዩ ልዩ የመዝናኛ አገልግሎቶች ማስፋፋትና ወጣቱን ተጠቃሚ ማድረግ፣

- በገጠር ልዩ ልዩ የወጣቶች መዝናኛ ማእከላት እንዲገነቡ ማድረግ፣ በማእከላቱ ውስጥ የሚገነቡ የመዝናኛ አገልግሎቶች ባህላዊና ዘመናዊ ሆነው በወጣቱ ምርጫ እንዲወሰኑና እየተስፋፉ እንዲሄዱ ማድረግ፣ በዚህ መሰረት የቤት ውስጥ መዝናኛ አገልግሎቶች፣ ተንቀሳቃሽ የፊልም አገልግሎቶች፣ ከቤት ውጭ የሚካሄዱ የውድድርና የስፖርት አይነቶች የሚስፋፉበት የመዝናኛ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ፣

- በትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉትን የመዝናኛ አገልግሎቶች ከትምህርት ቤት ውጭ ያሉ ወጣቶችም በእረፍት ቀናት እንዲጠቀሙባቸው ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- በገጠር በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና በየወረዳው በሚኖሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተጠናከረ የቤተመፃህፍትና የኮምፒውተር አገልግሎት መስጫ ማእከላት እንዲስፋፉ ማድረግ፣
- የወጣቶች መዝናኛ ተቋማት ባለቤትነት በወጣቱ እጅ እንዲሆንና ራሱ እያስተዳደራቸው የአመራር ብቃቱን የሚገነባበት ሁኔታ መፍጠርና የመዝናናት ሂደቱ የወጣቶችን ንቁ ተሳትፎና የማያቋርጥ እንቅስቃሴ (youth activisan) ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ፣
- ልዩ ልዩ አጋጣሚዎችን በመፍጠር ወጣቱ በተለያዩ የአመቱ ቀኖች በየቀበሌው ተሳትፎ የሚያደርግባቸው ትልልቅ የተሃድሶ እንቅስቃሴዎች ማደራጀት፣ ለዚህ ስራ የአመቱ የገበሬዎች ቀን፣ የሰራተኞች ቀን፣ የሴቶች ቀን፣ ግንቦት ሃያና የነፃነት ቀናትን እንዲሁም ሌሎች ባህላዊና ሃይማኖታዊ በአላትን በትልቅ ስነ ስርአት ወጣቱን በሰፊው ባሳተፈና ግንዛቤን በሚያዳብር መልኩ በድምቀት ማክበር፣ በአገርህን ኖወቅ ፕሮግራም የገጠር ወጣት ተሣታፊ እንዲሆን ማትረፅ፡፡

- የወጣቶች ቀን ተመድቦ በዚሁ መሰረት ወጣቱ በልዩ ልዩ ስነ ስርአቶችና ስልቶች እንዲያከብረው፣ በዚህ እለት ወላጆችና ህብረተሰቡ ለወጣቱ በአካልና በመንፈስ መጐልመስ የሚያበረክቱትን አስተዋፆኦ በተመለከተ ወይም የጋራ አቋም እንዲያዳብሩ ማድረግ፣
- በቀበሌዎች ውስጥ፣ ቀበሌ ከቀበሌ እንዲሁም ወረዳ ከወረዳ ወዘተ የገጠር ወጣቶች የስፖርት ውድድሮች የሚካሄዱበት ሁኔታ መፍጠር፣

## 1.2.4 የገጠር ወጣቶች የአካባቢ ጥበቃና መሬትን አረንጓዴ በማልበስ እንቅስቃሴ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ፣

- ወጣቶች የአካባቢ ጥበቃንና አካባቢን አረንጓዴ የማልበስ አስፈላጊነትን እንዲገነዘቡ ማድረግ፣ በራሳቸው ፈቃደኝነት መርሃ ግብር ቀርፀው አካባቢያቸውን በአረንጓዴ እንዲያለብሱ ማንቀሳቀስ፣
- አካባቢን አረንጓዴ የማልበስና የአካባቢ ጥበቃ እንቅስቃሴዎቹ በወጣቶች መካከል ሰፊ የውድድርና የስኬት መንፈስ የሚፈጥሩ፣ የተሳኩ ስራዎችን ለሰሩ ወጣቶች ሽልማቶችን በቡድንና በግለሰብ ደረጃ የሚያስገኙ እንዲሆኑ ማድረግ፣ ወጣቶች በዚህ መንገድ ያመጡትን ለውጥ ባለስልጣናት እየዞሩ በመጐብኘት የሚያበረታቱና እውቅና የሚሰጡበት፣

መገናኛ ብዙሃን በተሳከሩ ስራዎች ላይ ሰፊ ሽፋን የሚሰጡበትና ቡድኖችና ግለሰቦችን የሚያስተዋውቁበት ሁኔታ መፍጠር፣

### 1.2.5 መገናኛ ብዙሃን ለገጠር ወጣቶች የሚሆኑ ልዩ ልዩ አዝናኝ ፕሮግራሞችን እንዲቀርፁና ለወጣቶቹ በተመደቡ ጊዜዎች እንዲያቀርቡ ማድረግ፣

- መገናኛ ብዙሃን የገጠር ወጣቶችን የሚያዝናኑ ፕሮግራሞች በተለይ በገጠር ሰፊ ተደማጭነት ባላቸው ሬድዮዎች አማካኝነት ተከታታይ ስራ እንዲሰሩ ማድረግ፣
- ለዚህ ስራ እንዲበጅ በየዞኑ ማእከላት ጠንካራ የማህበረሰብ ሬድዮዎች እንዲቋቋሙ ማድረግ፣ ሬድዮ ጣቢያዎቹ ለገጠሩ ወጣት ሰፊ እድል የሚሰጥ ፕሮግራምና አመራር እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- የፌዴራልና ትልልቅ የክልል ሬድዮና ቴሌቪዥኖችም የወጣቱን ሁኔታ የሚገልፁና በወጣቱ ላይ ያተኮሩ ፕሮግራሞችን እያዘጋጁ እንዲያቀርቡ ማድረግ፣

## 1..3. የገጠር ወጣቶች ፖለቲካዊ ተሳትፎን በማጠናከር የመልካም አስተዳደር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣

አላማ፣

1. በገጠር መላውን አርሶ አደር ባሳተፈ አኳኋን ዴሞክራሲያዊና መልካም አስተዳደር የሰፈነበት አስተማማኝ ሁኔታ መፍጠር፣
2. ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር የሰፈነበት ሁኔታ ለመፍጠር በሚደረገው ጥረት የገጠር ወጣቶች የተደራጀና ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸውና ከሂደቱም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣

### 1..3.1 የገጠር ወጣቶች በመንግስትና በህብረተሰብ ደረጃ ልዩ ትኩረት እንዲሰጣቸው ማድረግ፣

- ወጣቶች ባሏቸው የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮች እንዲሁም በመፍትሄዎቹ ዙሪያ መንግስትና ህብረተሰቡ ከወጣቶቹ ጋር እየተመካከሩ የተሟላ የጋራ ግንዛቤና አቋም እንዲይዙበት ማድረግ፣ በተደረሰው የጋራ አቋም መሰረትም ወጣቱን የማይተካ ነገር ግን ደጋፊ ሚናቸውን በአግባቡ የሚጫወቱበት እንቅስቃሴ ማካሄድ፣
- መንግስት ወጣቶች የራሳቸውን ልዩ ልዩ መድረክ ለመክፈት የሚያደርጉትን ጥረት መደገፍና ማበረታታት፣ በመድረኮቹ በብቃት ለመጠቀም የሚያስችል የስልጠናና የአቅም ግንባታ ስራዎችን በመስራት እንዲደግፍ ማድረግ፣

- መንግስትና ህብረተሰብ በወጣቱ ላይ የሚፈፀሙ ማናቸውንም በደሎች በጋራ ለመመከት የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ መፍጠር፣ በዚህ ረገድ ወጣቶች የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በየጊዜው የሚያቀርቡበት ስርአት ማደራጀት፣

### 1.3.2 ወጣቶች በራሳቸውና በህብረተሰብ ጉዳዮች ላይ በሰፊውና በቀጥታ የሚሳተፉበት ሁኔታ ማመቻቸት፣

- ወጣቶች በየጊዜው በህብረተሰቡ ውስጥ የሚካሄዱ የልማት፣ የሰላምና የመልካም አስተዳደር ተግባራትን የሚያውቁና ከራሳቸው ጥቅም እየተነሱ የሚገመግሙበትና መስተካከልና መዳበር አለባቸው የሚሏቸውን ጉዳዮች የሚለዩበት ስርአት ማበጀት፣ ይህ ስርአት የወጣቶቹን አስተያየት በምክር ቤቶች አቅርቦ ለማፀደቅ የሚያስችል እንዲሆንም አድርጎ መቅረፅ፣
- ወጣቶች የራሳቸውን ችግሮች ለማቃለልና በራሳቸው ተሳትፎ ሊሰሯቸው የሚችሉ ነገሮችን ለመለየት የሚችሉበት መድረክ በቋሚነት ማመቻቸት፣ በዚህ መድረክ የሚኖረው የወጣቶች ተሳትፎ በተደራጀ አኳኋን እንዲሆን ማድረግ፣
- ወጣቶች በምክር ቤት መድረኮች በተወካዮቻቸው አማካይነት እየቀረቡ የራሳቸውን ፍላጎት የሚያስረዱበት

ሁኔታ ማመቻቸት፣ ምክር ቤቶች በወጣቶች በኩል የቀረቡ አስተያየቶችን መነሻ በማድረግ በእቅዳቸው ውስጥ የሚያካትቱበት፣ ተግባራቱን ለመፈፀም አስፈላጊ የባጀትና መሰል ድጋፎችን የሚያደርጉበት፣ ተግባራቱ በዝርዝር የስራ መርሃ ግብሩ ውስጥ ገብተው የሚፈፀሙበትን ሁኔታ ማረጋገጥና ወጣቶቹ በአፈፃፀም ጉዳይ ላይ ቀጥተኛና ሰፊ ተሳትፎ የሚያደርጉበት ሁኔታ ማመቻቸት፣

- መንግስት ከወጣቶች ጋር ወጣቶቹ በሚያነሷቸው ልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ እንዲሁም መንግስት ለወጣቶችም ሆነ ለመላው ህብረተሰብ ይጠቅማሉ ብሎ ባመጣቸው ልዩ ልዩ ሃሳቦች ወይም እቅዶች ላይ በአጋርነት (partnership) መንፈስ የሚሰራበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

### 1.3.3 ወጣቶች በነፃ የሚደራጁበት ሁኔታ መፍጠር፣

- ወጣቶች በመሰላቸውና ጥቅማችን ይበልጥ ያስጠብቅልናል በሚሉት መልክ እንዲደራጁ ሁኔታውን ማመቻቸት፣ በመንግስት በኩል ወጣቱ ቢደራጅባቸው ይጠቀማል ብሎ የሚያምንባቸውን የአደረጃጀት አይነቶች ለወጣቶች በዝርዝር አቅርቦ በራሳቸው ፈቃደኝነት እንዲደራጁበት ማገዝ፣
- የወጣቱ ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች በመቻቻልና በጋራ ጥቅም ዙሪያ በአንድ አሰባሳቢ የፌዴሬሽን መልክ ያለው

አደረጃጀት ዙሪያ እንዲሰባሰቡ ማድረግ፣ ፌዴሬሽኑ የሁሉንም ወጣት ማህበራት እኩል ተሳትፎ የሚያረጋግጥ እንዲሆን ማድረግ፣

- መንግስት የወጣቶች ማህበር እንዲጠናከር አመራሮቹን በማሰልጠንና በማንኛውም ቦታና ሁኔታ በአቻነት መንፈስ በመቅረብ ተባብሮ የመስራትን ባህል ማዳበር፣ መንግስት ማህበራቱን በምንም አይነት ሁኔታ እንደተላላኪ እንዳይመለከታቸው፣ የማህበራቱን ተግባራት ከራሳቸው ከማህበራቱ አባላት ፍላጐት ብቻ እንዲመነጭ ማድረግ፣ ማህበራቱ የሌላ ሶስተኛ ወገን ፍላጐት ማስፈፀሚያ እንዳይሆኑ ማድረግ፣ በየደረጃው ያለው የመንግስት አካል ሁሉንም የወጣቶች ማህበራት በእኩልነት የሚመለከትና የሚያስተናግድ እንዲሆን ማድረግ፣

## 1.3.4 በወጣቶች ላይ በቀጥታ የሚፈፀሙ የመልካም አስተዳደር መጓደልን የሚያመላክቱ ስህተቶችን በፅናት ታግሎ ማስወገድ፣

- ወጣቶችን እንደአጥፊና እንደተጠርጣሪ በመመልከት የሚደረጉ ማናቸውንም ነፃነታቸውን የሚገድብና የሚያሸማቅቃቸው እንቅስቃሴ መከታተልና ሲከሰቱም በጥብቅ ማስወገድ፣ በዚህ ረገድ በወጣቶች ላይ እንደዚህ አይነት በደሎች ሲያደርሱ የቆዩ ክፍሎች ካሉ በቅድሚያ

አመለካከታቸውን በማስተካከልና የተጠቀሱት አይነት ስህተቶች በፍፁም የማይፈቀዱ እንደሆኑ በማስገንዘብ እንዲታረሙ ማድረግ፣ ይህን ጥረት ባለመቀበል ስህተት የሚፈፅሙ ሲኖሩ በህግ እንዲጠየቁና እንዲታረሙ ማድረግ፣ ይህ ስራ በወጣቱ ዘንድ የህግ አክባሪነትና መብትን በዴሞክራሲያዊ መንገድ የማስከበር አመለካከት እንዲዳብር በሚያደርግ አቅጣጫ እንዲፈፀም ማድረግ፣

- ለወጣቱም ሆነ ለመንግስት ህግ አስከባሪ አካላት እንዲሁም ለህብረተሰቡ በወጣቱ አያያዝ ጉዳዮች ላይ የማያቋርጥ የግንዛቤ ማሳደግ ስራ መስራት፣

www.abyssinialaw.com

# ያአል 4

# በፖኬጁ ትግበራ፣ ክትትልና ግምገማ የወጣቱና የመንግሥት ሚናና ድርሻ፣

## 1. በፓኬጁ ትግበራ፣ ክትትልና ግምገማ የወጣቶች ሚናና ትርሻ

የወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን በመአ ታት በልማት፣ በሰላም፣ በመልካም አስተዳደርና በዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ የሚኖራቸውን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የወጣቶች ብሔራዊ ፖሊሲን መሠረት አድርጐ በወጣቶች ተሳትፎ የተቀረናውን የወጣቶች የእድገት ፓኬጅ በተሟላ ሁኔኖ ተፅባራዊ ለማድረግ ዋነኛው ስትራቴጂክ ኃይል ራሱ ወጣቱ እንደመሆኑ መጠን ከፌዴራል ጀምሮ እስከ ቀበሌ ደረጃ ድረስ ህገ-መንግሥቱ በፈጠረለት ምቹ ሁኔታ በልዩ ልዩ ህጋዊ ዓላማዎችና የአደረጃጀት ቅርፆች ዙሪያ እየተደራጀ የፓኬጁን አፈፃፀም ከመንግስት የልማት ስትራቴጂዎች ጋር አስተሳስሮ በብቃት እንዲመራ፣ እንዲፈፅምና እንዲያስፈፅም ይጠበቃል:: በመሆኑም በፓኬጁ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ወጣቶች ተደራጅተው ሲንቀሳቀሱ የሚኖራቸው ተግባርና ኃላፊነት/ሚና ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፣

1. በፓኬጁ አተገባበር ወጣቱ ወሳኝ ስትራቴጂያ ኃይል መሆኑን ተገንዝቦ በተደራጀ አኳኋን በሀገሪቱ የልማት እንቅስቃሴና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያስችሉ የግንዛቤ ማሳደጊያና የኘሮሞሽን ኘሮግራሞችን በመቅረፅ የማነሳሳት፣ የማስተማር፣ የማሳወቅና የማደራጀት ተግባራትን ያከናውናሉ፣

2. በልዩ ልዩ ዓላማዎች ዙሪያ በተደራጁ ማህበራትና ክበባት መካከል ኔትወርኮች እንዲፈጠሩ በማስቻል የወጣት ማህበራትና ክበባት ውስጣዊ ነፃነታቸውን ጠብቀው ከቀበሌ ጀምሮ በየደረጃው በፌዴሬሽን እንዲደራጁና በአንድ አገር አቀፍ የወጣት አደረጃጀቶች ፌዴሬሽን ጥላ ሥር እንዲሰባሰቡ ያደርጋሉ፣
3. የኢትዮጵያ የወጣት አደረጃጀቶች ከአህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ አቻዎቻቸው ጋር በትብብር፣ በሶሊዳሪቲና በአጋርነት የሚሠሩበትን አግባብ ያመቻቻሉ፣
4. የወጣት አደረጃጀቶች የአባላትን አቅም ለማጐልበት የሚያስችሉ የስልጠና፣ የአሠራርና የአደረጃጀት ስልቶችን በመቀየስ ከአጋር አካላት የአቅም ግንባታ ድጋፍ የሚገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻሉ፤ የአባላትን የመፈፀም አቅም የሚያሣድጉ ተግባራትን ያከናውናሉ፣
5. በየደረጃው የሚቋቋሙ የወጣት አደረጃጀቶች ወጣቶቹን በማነሣሣትና በማስተባበር በበጐ ፈቃድ አገልግሎት ኘሮፅራም ላይ እንዲሠማሩ ጸደርፉሉ፣
6. የወጣት አደረጃጀቶች ለፓኬጁ ትግበራ ከወጣቱ የሚጠበቀውን ሀብት መላው ወጣት እንዲያበረክት ያነሣሣሉ፣ ተግባራዊ ሂደቱንም ያስተባብራሉ፣
7. የወጣቱን ሁለንተናዊ ተሳትፎ የሚያረጋግጡ ቋሚ መድረኮችን በማዘጋጀት ወጣቱ በአገሪቱ የልማት እንቅስቃሴና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በስፋት እንዲሳተፍ ያደርጋሉ፣ ተጠቃሚነቱም መረጋገጡን ይከኖ ተላሉ፣

8. በወጣቱ ላይ የሚፈፀሙ የመልካም አስተዳደር በደሎችን መንስኤ፣ ዓይነትና መጠን በመለየት በሚመለከታቸው የፍትህና የዲሞክራሲ አካላት አማካይነት እንዲወገዱ ይታገላሉ፣
9. የልምድ፣ የተሞክሮና የመረጃ ልውውጥ መድረኮችንና ኘሮግራሞችን በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደርጋሉ፣ ያገኙትንም ውጤት እየተከታተሉ ይመዝናሉ፣
10. የወጣት አደረጃጀቶች በየደረጃው ቀርፀው ለሚተገብሯቸው ልዩ ልዩ ኘሮግራሞች ማስፈፀሚያ ሪሶርስ ሞቢላይዝ ያደርጋሉ፣ አጠቃቀሙን ይከታተላሉ፣ ቀጣይነቱንም ያረጋግጣሉ፣
11. በፓኬጁ ውስጥ የገጠር ወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተቀመጡትን፣
    - ወጣቶችን በቤተሰብ መሬት ላይ ተሣታፊና ተጠቃሚ የማትረፅ፣
    - በየቀበሌው ሊታረሱ የሚችሉና በማንም ያልተጸዙ የኖርሻ መሬቶችን ለወጣቱ በማከፋፈል፣ ወጣቶች በተራራ ልማት ላይና ኮሜርሻል ዋጋ ባላቸው የአግሮ ፎረስትሪና የእንስሳት ሀብት ልማት ላይ እንዲሠማሩ በማትረፅ፣
    - ወጣቶች በሠፈራ ኘሮፅራም እንዲሠማሩ በማነሣሣት እና
    - ከግብርና ውጪ ባሉ የልማት መስኮች ላይ ተሠማርተው የገቢ አቅማቸውን እንዲያሣድጉ የማነሣሣት፣ ግንዛቤያቸውን የማሣደግና በየደረጃው ከሚገኙ አስፈፃሚ አካላት ጋር ተቀናጅተው በመሥራት መላው ወጣት ተጠቃሚ እንዲሆን ያደርጋሉ፣

በተመሣሣይ ሁኔታ የከተማ ወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አኳያ:-

- ወጣቶች በአነስተኛና ጥቃቅን የልማት ዘርፎች፣
- በኮንስትራክሽን ልማት፣
- በከተማ ግብርና ልማት፣
- በእደ ጥበብና በፈጠራ ሥራዎች ላይ ተሠማርተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማነሣሣት፣ ግንዛቤያቸውን የማሣደግና ቅንጅታዊ አሠራሮችን የማዳበር ተግባራትን ያከናወናሉ፣

- የገጠርና የከተማ ወጣቶችን ሰብዕና ለመቅረፅ የሚያስችሉ ተቋማትን ለመገንባት፣ ለማስፋፋትና የተሟላ አገልግሎት እንዲሠጡ ለማድረግ በሚካሄደው እንቅስቃሴ ወጣቶች ከአስፈፃሚ አካላት ጋር ተባብረው የእውቀት፣ የጉልበትና የፋይናንስ አስተዋፅዖ እንዲያደርጉ ያነሣሣሉ፣ ጸስተባብራሉ፣
- የገጠርና የከተማ ወጣቶችን ፖለቲካዊ ተሣትፎ ለማረጋገጥ በሚካሄዱ የእቅድ ዝግጅት፣ የትግበራና የግምገማ ሥራዎች ላይ ተደራጅተው እንዲሣተፉ እንዲሁም በህዝብ ምክር ቤቶች ውስጥ በየፌዴሬሽኖቻቸው አማካይነት ተገቢውን ውክልና እንዲያገኙ የማነሣሣት፣ የማደራጀት፣ የማስተባበርና ሂደቱን የመከታተል ተግባራትን ያከናውናሉ፣ በዚህም ረገድ ከሁሉም የልማት ኃይሎች ጋር ፓርትነርሺፕ በመፍጠር የመሪነት ሚናቸውን በብቃት ለመወጣት የሚያስችሉ የልማትና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ተግባራትን ያከናወናሉ፣

12. ወጣቶችን በልማት፣ በሰላም፣ በመልካም አስተዳደርና በዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በስፋት ተሳታፊና ተጠቃሚ ለማድረግ

www.abyssinialaw.com

የሚያስችሉ የማደራጀት፣ ግንዛቤያቸውን የማሣደግ፣ ተሞክሮና ልምድን የመቀመር፣ የቴክኒክ ድጋፍ የመስጠትና ወጣቱን የማብቃት ተግባራትን ያከናወናሉ፣

## 2. በፓኬጁ ትግበራ ፣ ክትትልና ግምገማ ረገድ የመንግስት ሚናና ድርሻ

የወጣቶችን የእድገት ፓኬጅ በየደረጃው ተግባራዊ በማድረግ የወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተሣትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በፓኬጁ በተቀመጡት ስትራቴጂዎች መሠረት መንግሥት የደጋፊነት ሚና እንደሚኖረው በግልጽ የተመለከተ በመሆኑ የወጣቶች ልማት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸው ልዩ ልዩ የመንግሥት አስፈጻሚ አካላት በፓኬጁ ትግበራ የሚኖራቸውን ድርሻ ለይቶ ማመላከት ተገቢ ነው ። ስለሆነም እያንዳንዱ የመንግሥት አስፈጻሚ ተቋም በፓኬጁ ትግበራ የሚኖረውን ድርሻ ከራሱ ሴክተር የልማት ስትራቴጂ ፉር አስተሳስሮ በመፈጸም ለፓኬጁ ስኬትና ለወጣቶች ሁለንተናዊ ብቃት መረጋገጥ የበኩሉን ሚና በብቃት እንደሚጫወት ይታመናል። በዚህም መሠረት በፓኬጁ አፈጻጸም የእያንዳንዱ የመንግሥት አስፈጻሚ ተቋም ሚናና ድርሻ ቀጥሎ ቀርቧል።

## 1. የፓኬጁን ውጤታማና ስኬታማ አተገባበር በብቃት ከማስተባበር አኳያ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ሚና ፣

1.1. በፓኬጁ አፈጻጸም ረገድ በየደረጃው ለሚሣተፉ የወጣት አደረጃጀቶችና አጋር አካላት በወጣቶች ተሣትፎ፣ በወጣት ማዕከላት፣ በሥልጠና ተቋማትና በስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ልማት አገልግሎት አሰጣጥና ማኔጅመንት፣ በሪሶርስ ሞቢላይዜሽን፣ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ኘሮግራም አፈጻጸም፣ በሰው ኃይል ልማት ፣በአሠራርና በአደረጃጀት ዙሪያ የአቅም ግንባኖ ትፉአ ጁሰጣል፣

1.2. የወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በየደረጃው በሚገኙ የልማት ኃይሎች የሚከናወኑ ወጣት ተኮር ተግባራትን ያስተባብራል፣ይከኖ ተላል፣ጁቶመፅማል፣

1.3. በፓኬጁ ይዘትና አተገባበር ረገድ ወጣቶችን ጨምሮ የሁሉንም የልማት ሀይሎች ግንዛቤ ለማሳደግና ብሔራዊ መግባባትን ለመገንባት የሚያስችል የግንዛቤ፣ የኘሮሞሽንና የሶሻል ሞቢላይዜሽን ኘሮፅራም ቀርጾ ተፅባራዊ ጸደርፉል

1.4. ወጣቶች በአካባቢና በማህበረሰብ ልማት ፣ በተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ፣ ኤች. አይ. ቪ/ ኤድስን በመከላከልና በሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት፣ በትምህርትና በማህበራዊ ደህንነት አገልግሎት ተግባራት ላይ በበጎ ፈቃደኝነት መርህ የሚሳተፉበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ሂደቱን ያስተባብራል፣ የቴክኒክ ድጋፍ ጁሰጣል፣

1.5. ወጣቶች በመረጡት ሕጋዊ ዓላማ ዙሪያ በሕገ-መንግሥቱና በፖሊሲው ማክቀአ ውስዓ እንዲደራጁ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣ የተደራጁትም በአንድ ሀገር አቀፍ ፌዴሬሽን ሥር እንዲሰባሰቡ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣ ፌዴሬሽኑም የቴክኒክ፣ የማቴሪያልና የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኝበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙንም ያስተባብራል፣ ይከኖ ተላል ፣

1.6. ልዩ ልዩ ወጣት ተኮር ቅኝቶችንና ጥናቶችን ያካሂዳል፣ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ሀገር አቀፍ የወጣቶች ዳኖ ቤዝ ጁመሠርኖ ል፣

